# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 87 ጥር 6 2002 ዓ.ም

**ከሰሞኑ የወያኔን ሰፈር ያናጋዉና መለስ ዜናዊን የአደባባይ ላይ ተሳዳቢ ያደረገዉ ይሄዉ የነፃነት ኃይሎች በተለይም የግንቦት ሰባት የነፃነት፤ የፍትህና፤ የዲሞክራሲ ንቅናቄ በአገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ በፍጥነት እየተጠናከረ መምጣት ነዉ።**

ዝርዝሩን ገጽ 3 ያንብቡ

## ወያኔ የግንቦት 7ትን እንቅስቃሴ ለመሰለል ከፍተኛ የሆኑና ልምድ አላቸው የተባሉ የደህንነት አባለቱን ወደ ውጭ አገር ማሰማራቱ ታወቀ

ከጊዜ ወደ ጊዜ ለወያኔ ትልቅ ራስ ምታት እየሆነ የመጣውን የግንቦት7ትን እንቅስቃሴ ለመሰለል፣ ወያኔ ታማኝ ያላቸውን የደህንነት አባላት ወደ ውጭ አገር ማሰማራቱን ከደህንነት አካባቢ ያገኘነው መረጃ አመለከተ። ወያኔ በርካታ የደህንነት አባለቱን ያሰማራው በውጭ አገር ላቋቋመው የስለላ ተቋሙ በቂ የሰው ሀይል ለመመደብ ሲሆን፣ በተለይ ከግል ጤና ጋር በተያያዘ ችግር አለባቸው ተብለው የታመኑ አባሎቹ እግረመንገዳቸውን ህክምናቸውን እየተከታተሉ ግንቦት7ትን ለመሰለል የተቋቋመውን መዋቅርም እንዲያግዙ መመደባቸው ታውቋል። አሁን በውጭ አገር የተመደቡት ሰዎች ቅንጅትን ለማፍረስ ከፍተኛ የሆነ ሚና ተጫውተዋል የተባሉ የትግራይ ተወላጅ የደህንነት አባላት ሲሆኑ፣ በውጭ አገር ሲሰማሩም በተቻላቸው መጠን ሁሉ ግንቦት 7ትን ሰርስረው በመግባት ንቅናቄው ከሁለት እንዲከፈል እንዲያደርጉ፣ ዋና ዋና ተሳተፊ የሚባሉትን መዝግበው እንዲይዙና የውጩንና የአገር ውስጡን ግንኙነት ለመበጠስ የሚያስችሉ ስራዎችን እንዲሰሩ የቤት ስራ ተሰጥቷቸዋል።

የደህንነት የመረጃ ምንጮቻችን እንደገለጹት በደህንነት መስሪያ ቤት ውስጥ ከዚህ በፊት የሬዲዮ መምሪያ ሀላፊ ሆኖ ሲሰራ የነበረው አለምሰገድ ተክለሀይማኖት የተባለው የህወሀት አባል ግንቦት7ትን ለመሰለል እንዲችል በለንደን ከተማ ተመድቧል። ግለሰቡ የጎረቤት አገሮችን የሬዲዮ ግንኙነት ሲጠልፍ የነበረና ኮድ ወይም መለያዎችን በመስበር መረጃዎችን ሲያጠናክር የነበረ ሲሆን፣ አዲስ የተሰጠውም ግዳጅ የግንቦት7ትን እንቅስቃሴ መሰለል፣ ሰዎችን ሰርጎ በማስገባት ወይም አባል በማድረግ ንቅናቄውን መከፋፈል የሚል መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል። **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወ/ት ብርቱካንና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ ጠየቁ

በአሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል አባላት ጋር በጋራ በመሆን ወ/ት ብርቱካንንና ሌሎችን የፖለቲካ እስረኞች ያስታወሱ ሲሆን፣ በለንደን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ደግሞ የእንግሊዝ መንግስት ወ/ት ብርቱካንንና ሌሎች እስረኞች እንደፈቱ ጥረት እንዲያደርግና ከዲሞክራቲክ ሀይሎች ጎን እንዲቆም ጥሪ አስተላልፈዋል።

ኢትዮጵያውያኑ የአምባገነኑን መለስ ዜናዊ አገዛዝ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ያጋለጡ ሲሆን፣ የውጭ መንግስታት እነዚህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እየተመለከቱ ዝምታን መምረጣቸውን ተቃውመዋል።

ግንቦት7 የወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳን የግፍ እስር አጥብቆ ማውገዙ ይታወሳል።

## የወያኔ ካድሬዎች በርካታ የደሀ አርሶ አደር የእርሻ መሬቶችን እየቀሙ መሆናቸው ተዘገበ

በምእራብ የአገሪቱ ክፍሎች የሚደረገውን አደገኛ የመሬት ነጠቃ እርምጃ አስመልክቶ ሪፖርተራችን እንደዘገበው፣ በግብርናው መስክ እንሰማራለን ብለው ፈቃዳቸውን የገለጹ በአዲስ አበባ ተቀማጭ የሆኑ የአገዛዙ ታማኝ ካድሬዎች፣ ወደ ገጠሪቱ የአገሪቱ ክፍል በመሄድ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ከደሀው ገበሬ ላይ በመንጠቅ ላይ ናቸው። ካድሬዎቹ ለይስሙላ በጣም አነስተኛ የሆነ የካሳ ገንዘብ እንደሚከፍሉ የጠቆመው ሪፖርተራችን፣ በአነስተኛ ገንዘብ ያገኙትን ሰፋፊ መሬቶች መልሰው ለውጭ አገር ባለሀብቶች በማከራየት በመካከሉ ከፍተኛ የሆነ ገቢ ሀብት በማካበት ላይ ናቸው። በአዲስ አበባ ዙሪያ ለኢንዱስትሪ ልማት ተብለው ከደሀው አርሶ አደር የተዘረፉት ቦታዎች ገንዘቡ ላለቸው ባለሀብቶች ከተሸጡ በሁዋላ፣ ባለሀብቶችም በቦታው እንዱስትሪ ሳይሆን ህንጻዎችን እንደሚገነቡባቸው ታውቋል። ያገዛዙ ታማኝ ካድሬዎች በዚህ አይነት ዘዴ በአንድ ቀን ሚሊየነር ደረጃ እየደረሱ መሆናቸውን የገለጸው ዘጋቢያችን፣ የወያኔ ከፍተኛ ሹሞችም ከዝርፊያው በስተጀርባ እንደሚገኙበት ጠቁሟል።

መለስ ዜናዊና አዜብ መስፍን በዋናነት የሚመሩት **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢፒአር ስም በርካታ ካድሬዎች እየተሰገሰጉ ነው

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ወኪላችን እንደዘገበችው ቢፒአር ተብሎ በሚጠራው ሰራተኛ የማፈናቀያ መንገድ ስም ለአገዛዙ አልተመቹም የተባሉ ሰዎች እየተነሱ በቦታቸው ታማኝ ካድሬዎች በመሰግሰግ ላይ ናቸው። የዩኒቨርስቲውን መዋቅር ሂደት በቀጥታ የሚመራው በመለስ ዜናዊ ሲሆን፣ የዩኒቨርሲተው ማህበረሰብ አባላት ምንም ተሳትፎ እንደማያደርጉ ታውቋል።

ዘጋቢያችን በላከቸው መረጃ መሰረት፣ በመዋቅር ስም ስራውን የሚሰሩት የእንድሪያስ እሸቴ ታማኞች ሲሆኑ፣ እንድሪያስም ቀጥተኛ ትእዛዝ የሚቀበለው ከመለስ ዜናዊ ነው። ከዚህ ቀደም የተለያዩ ትምህርት ክፍሎች ሀላፊዎች የሚመደቡት በዩኒቨርስቲው አባላት የነበረ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ግን ማንኛውም ሹመት የሚሰጠው በቀጥታ በእንድርያስ እሸቴና በመለስ ዜናዊ መሆኑን ዘጋቢአችን ጠቅሳለች። ዲሞክራሲ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተቀብሮዋል የምትለው ዘጋቢአችን፣ ቀብሩን ያስፈጸመው ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ በአእምሮና በአካል እየተዳከመ የመጣው እንድርያስ እሸቴ መሆኑን ገልጻለች።

በአሁኑ ጊዜ በአገራችን በርካታ ወንጀሎች በመለስ ዜናዊና ግብራበሮቹ ሲፈጸም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለምን ዝም ብለው ይመለከታሉ ተብላ ለተጠየቀችው ስትመልስ "ዋናው ምክንያት ተማሪዎች ከተመረቁ በሁዋላ ለመቀጠር እንዳይቸገሩ ሰግተው ነው። ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ትምህርታቸው ወቅት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በሙሉ ይመዘገባል። መንግስትን የሚቃወሙ ተማሪዎች ስራ አያገኙም። ይህንንም በመፍራት ተማሪዎቹ ዝምታን መርጠዋል። በሌላ በኩልም እንታሰራለን፣ እንገደላለን ብለው የሚፈሩ ተማሪዎች አሉ።" ስትል አስተያየቷን ሰጥታለች።

በሌላ በኩል በተጠናከረ መረጃ እንደተመለከተው ደግሞ የተማሪውን የቀን ተቀን ውሎ የሚመዘግቡት የትግራይ ተወላጅ ተማሪዎችና በተማሪ ስም የተሰገሰጉ የትግራይ ተወላጅ ካድሬዎች ሲሆኑ፣ እነዚህ ካድሬዎች ከዩኒቨርሲቲው የጥበቃ አባላት ጋር በመተባበር፣ የደህንነት ስራ በመስራት ላይ እንደሚገኙ ታውቋል። ተማሪዎቹ በአገራቸው የሚካሄደውን የመሬት ዝረፊያ፣ ድህነት፣ አምባገነንነትና የመብት ረገጣዎች፣ የአገር ክዳት ወንጀሎችና ዘረኝነት ሲስፋፋ እንዳላዩ ሆነው ለማለፍ የተገደደዱት አገዛዙ በዘረጋው የስለላ መረብ የተነሳ ነው። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከትምህርት ተቋምነቱ ይልቅ የካድሬ መፈልፈያ መሆኑን በርካቶች ይስማሙበታል።

## በትግራይና በኦሮሞ ተማሪዎች መካከል በተፈጠረ የዘር ግጭት የሰው ህይወት አለፍ

በአርሲ ዞን በሚገኘው አርዳኢታ የቴክኒክ ሙያ ኮሌጅ በተፈጠረው የዘር ግጭት ተማሪዎች በፖሊስ ጥይት መገደላቸውን ሪፖርተራችን ዘግቧል። በግቢው የሚገኙ ተማሪዎችን አነጋግሮ እንደዘገበው አንዱ ተማሪ በተተኮሰበት ጥይት ወዲያው ህይወቱ ሲያልፍ ሌሎች ሁለት ተማሪዎች ግን ጥር 2 ቀን በቂ ህክምና በማጣት ህይወታቸው አልፎአል። ዘጋቢአችን እንደገለጸው ጠቡ የተለመደው የትግራይ ተማሪዎች በተማሪ ኮሚቴዎች ውስጥ የበላይነትን መያዛቸውን ተከትሎ ይቀስቀስ እንጅ፣ የዘር ጉዳይ ግቢውን ለበርካታ ወራት ሲያወዛግብ መቆየቱን ጠቅሷል። በአርኢዳኢታ ኮሌጅ ውስጥ የትግራይ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ትተው የደህንነት ስራ ላይ መሰማራታቸው በርካታ ተማሪዎችን ያበሳጭ እንደነበር የገለጸው ዘጋቢያችን፣ ተማሪዎችም ከትግራይ ተማሪዎች ጋር የሚያደርጉትን ማንኛውንም አይነት ግንኙነት አቋርጠው እንደነበር አስታውሷል። ጸቡ በተፈጠረበት ወቅት የሁሉም ብሄር ተወላጅ ተማሪዎች በአንድነት በጽናት ቆመው የፖሊስን ዱላ ለመቋቃም የቻሉ ሲሆን፣ የትግራይ ካድሬ ተማሪዎች ግን ከፖሊሶች ጋር መቆምን እንደመረጡ ተማሪዎችን ዋቢ አድረጎ ዘጋቢአችን ጠቅሷል።

እስካሁን ድረስ ትምህርት አለመጀመሩ የታወቀ ሲሆን፣ ተማሪዎች ያላግባብ እንዲባረሩ የተወሰነባቸው ተማሪዎች ካልተመለሱ በስተቀር ትምህርት አንጀምርም ማለታቸውም ታውቋል። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ዩኒቨርሰቲዎች እየታየ ያለው የዘር ግጭት ወደ ከፋ ደረጃ እየተሸጋገረ መምጣቱን ባለፈው ሳምንት በጎንደር ዩኒቨርሰቲ የተከሰተውን፣ ፣ እንዲሁም በባህርዳር፣ በአዳማና በሌሎችም ዩኒቨርስቲዎች የሚታዩትን ችግሮች ዋቢ **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

# ርእሰ አንቀጽ

## የተቀናጀ የሕዝቦች ትግል በአፍሪቃ ቀንድ እየተስፋፋ የመጣውን አለመረጋጋትና የአክራሪነት አደጋን ማክሸፊያ አስተማማኝ መሣሪያ ነው!

የአፍሪቃ ቀንድ የደህንነት ችግሮች ተወሳስበው አሁን አስጊ ደረጃ ላይ ደርሰዋል። እናት አገራችን ኢትዮጵያ የክልሉ ሰላምና መረጋጋት መሠረት መሆን ይገባት ነበር። በተግባር እያየነው ያለው ሃቅ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። ምክንያቱ ግልጽ ነው። ኢትዮጵያ ከጠባብ የቡድን ፍላጎት በላይ አርቆ ማየት በማይችል እና በራስ መተማመን የተሳነው የአናሳ ዘረኛ አገዛዝ ሥር በመውደቋ የመፍትሄ ምንጭ መሆኗ ቀርቶ የችግሩ አባባሽ ሆናለች። ይህ ሃቅ እጅግ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን አስቸኳይ መፍትሄ ካልተበጀለት መዘዙ የከፋ ይሆናል።

የወያኔ የውጭ ጉዳይ ፓሊሲ የሃገር ውስጥ የአስተዳደር ፖሊሲው ተቀጥያ ነው። ሁለቱም የሚመነጩት በጉልበት የያዘውን የአናሳ አምባ ገነን ስልጣን በብዙሃኑ እንዳይነጠቅ ለመከላከል ከተሰራ ስሌት ነው። ይህም ***ተቀናቃኞችን እርስ በርስ በማጋጨት የማዳከም እና ገላጋይ ሆኖ የመቅረብ ስልት*** ነው። ወያኔ በዚህ እኩይ ስልቱ ተጠቅሞ አካባቢውን በማመስ ቀጠናው ከእኛ አልፎ የመላው ዓለም የስጋት ምንጭ እንዲሆን አድርጓል።

የአፍሪቃ ቀንድን ወደ ስጋት ቀጠናነት የቀየሩት ኩነቶች በሙሉ የወያኔ መሰሪ እጅ አለባቸው። ከፋሺስት ጣልያን ወረራ ወዲህ ትልቁን የሕይወትና የንብረት ኪሳራ ያደረሰብን ከኤርትራ ጋር የተደረገው አሳፋሪ ጦርነት በሁለቱ አገሮች ሕዝቦች መካከል ቂምና ጥርጣሬን በመትከል ለሁለቱም ሕዝቦች ለማይበጁ የቅርብና የሩቅ ኃይሎች እንድንመች አድርጎናል። ጦርነቱ ራሱ የፈጠራቸው በርካታ ችግሮች ቢኖሩም በተለይም ከሄይጉ የዳኝነት ብይን ወዲህ ያለው ጦርነትም ሰላምም የሌሉበት እና ዘወትር በዓይነ–ቁራኛ መጠባበቅ ያሳደሩት አሉታዊ ተጽዕኖ መላውን የአካባቢውን አገሮች አዳርሷል። ይህ ሳይበቃ መለስ ጌቶቹን ለማስደሰት እግረ መንገዱንም የአገር ውስጡን ችግር ለማረሳሳት በሶማሊያ ያደረገው ጣልቃገብነት የአካባቢው የደህንነት ችግሮች እጅግ እንዲባባሱና ዓለም ዓቀፋዊና ሃይማኖታዊ ይዘት እንዲላበሱ አድርጓል። በወያኔ ጣልቃገብነት ሳቢያ ሶማሊያዊያን ጎረቤቶቻቸን ሳይወዱ ወደ አክራሪነት ተገፍተዋል፤ በኢትዮጵያም ላይ ዘላቂ ቂምን እንዲቋጥሩ ተገደዋል። የወያኔ የሶማሊያው ጀብደኝነት በየመን እየተስፋፋ ከመጣው የአክራሪነትና የምሬት ንቅናቄ ጋር በብዙ ክሮች ተያይዟል። ወያኔ በኦጋዴን ወገኖቻቸን ላይ እያደረሰ ያለው ፍጅትም ለአካባቢው ችግር ተጨማሪ ማቀጣጠያ እየሆነ ነው። በአጠቃላይ ከሄይጉ ብይንና በሶማሊያ ከተደረገው ጣልቃ ገብነት ወዲህ የአፍሪካ ቀንድ ጂኦፓለቲካ ፈጽሞ ተቀይሯል። አካባቢው የሥርዓተ አልበኝነትና የአክራሪነት ምንጭ እየሆነ ነው።

ወያኔ ለዚህ ስጋት እየሰጠ ያለው ምላሽ ደግሞ ችግሮቹን የባሰ የሚያወሳስቡ ናቸው። ዳር አገሩን ገምሶ በመስጠት የሱዳን መንግሥት ወዳጅነትን ለመግዛት እየጣረ ቢሆንም ይህ ራሱን የቻለ ሌላ ውስብስብ ቅራኔ መፍጠሩ የማይቀር ነው። የሱዳን አገራዊ አንድነት ጉዳይ ገና ያለየት በመሆኑ ወያኔ ከሁሉም የሱዳን ኃይሎች ጋር በመሞዳሞድ ላይ ይገኛል፤ ይህም ሌላ የቅራኔ ምንጭ ሊሆን ይችላል። ለግብጽና ጂቡቲ መሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ደግሞ ልክ እንደ ራሱ ወታደራዊ ሹማምንትና የድርጅት አባላት ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን በጉቦነት በመስጠት ድጋፋቸውን ለመግዛት የሚያደርገው መራወጥ አክራሪነትን እቤት ድረስ መጋበዝ ሊሆን ይችላል።

ምዕራባዊያን አርቀው ለማየት ባለመፈለጋቸውና እና በአጭር ግዜ መፍትሄ ፍለጋ ላይ በመጠመዳቸው ወያኔ አካባቢውን በማመስ እሱ ብቻ የመረጋጋት ኃይል መስሎ እንዲታይ የሚያደርገውን ማጭበርበር መገንዘብ የቻሉ አይመስልም። በዚህም ምክንያት እውነተኛው የችግሩ ምንጭ መፍትሄ መስሎ የሚቀርብበት ታላቅ አደጋ ተጋርጦብናል። ምዕራባዊያን መንግሥታት የወያኔ የብልጠት ጨዋታ አለመገንዘባቸው ብቻ ሳይሆን ወያኔ ይጠቅመናል ብለው ለማሰባቸው በርካታ አመላካቾች አሉ። ከሁሉም በላይ ገላጭ አመላካች ግን በኤርትራ ላይ የተጣለው ፈሩን የሳተ ማዕቀብ ነው። ይህ ማዕቀብ ለወያኔ የልብ ልብ በመስጠት የአደጋውን መጠን ያገዝፈዋል የሚል ፍራቻ አለን። ካሁኑ መለስ ጉልበትና ሃብት ካላቸው አገሮች መሪዎች ጋር ፎቶ ለመነሳት እና የራሱን ተክለ ሰውነት ለመገንባት በአፍሪካና አውሮፓ ሕብረቶች እና በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ ደፋ ቀና ሲል ይታያል። ምዕራባዊያን ከቀንደኛው አሸባሪ ወያኔ ጋር አብረው በገቡበት ሽርክና ሳቢያ መውጣት ከማንችልበት የቅራኔዎች አዘቅት ውስጥ ልንገባ እንችላለን ብለን እንሰጋለን።

የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች አስቸኳይ የጋራ መፍትሄ ካልፈለጉ በስተቀር የአካባቢው ደህንነት መደፍረስ የሁለቱንም አገሮች ህልውና ክፉኛ መፈታተኑ አይቀርም። ስለሆነም የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች የጋራ ለሆነው ዘላቂ ጥቅማቸው መከበር በአንድነት መቆም ይኖርባቸዋል። ከሁሉ አስቀድሞ ለአካባቢው ሰላም መደፍረስ መሠረታዊ ምክንያት የሆነው ወያኔ በኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች የጋራ ትግል መወገድ ይኖርበታል።

የአፍሪካ ቀንድን ከምሬትና ከአክራሪነትነት ነፃ ማድረግ ከኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች የዘለቄታ ጥቅም ጋር በጽኑ ይተሳሰራል ብሎ ግንቦት7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በጽኑ ያምናል። ይህንን ዓላማ ለማሳካት ሁለቱም ሕዝቦች በጋራ የመታገል ግንባር ቀደም ኃላፊነት አለባቸው ብሎም ያምናል። በአካባቢው ለሽብርተኝነት መስፋፋት ዋናኛው ምክንያት ደግሞ የወያኔ አገዛዝ በመሆኑ የፀረ–ሽብርተኝነት ትግላችን ቀዳሚ ዒላማችን ራሱ ወያኔ መሆን ይኖርበታል። ግንቦት7 የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች ለዘላቂ የጋራ ጥቅሞቻቸው ሲሉ በመለስ አገዛዝ፣ በሱም ሳቢያ እየተስፋፉ የመጡትን አለመረጋጋትን፤ ምሬትንና አክራሪነትን በጋራ መዋጋት እንዳለባቸው ያምናል፤ ይህንን የጋራ ትግል እውን ለማድረግም ተግቶ ይሠራል።

**ሽንፈት ለቀንደኛው አሸባሪና ዘረኛው ወያኔ !!!**

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## ወያኔ የግንቦት 7ትን እንቅስቃሴ ለመሰለል ከፍተኛ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ሲራክ አሰፋ የተባለው ሰላይ ደግሞ ከዚህ በፊት በደህንነቱ የሬዲዮ መምሪያ ስር ሲሰራ የነበረ ና የተቃዋሚ ድርጅቶች አባለት በሬዲዮ፣ በጋዜጣና በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን የሚያሰራጩዋቸውን መረጃዎች እየተከታተለ ሲይዝና ሲያጠናክር የነበረ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ በሳኡዲ አረቢያ ተመድቦ በአረብ አገራት ያለውን የግንቦት7ትን እንቅስቃሴ እንዲሰልል ሀላፊነት እንደተሰጠው መረጃው አመልክቷል።

ካሳየ ገብረመድህን የተባለው ሌላው ሰላይ ደግሞ ከዚህ በፊት የተለያዩ ድህረገጾች ሲያወጧቸው የነበሩትን ጽሁፎችና በአገርውስጥና በውጭ አገር የሚታተሙ ጋዜጦችን እየተከታተለ ይዘታቸውን ለበላይ አለቆቹ ሲያቀርብ የነበረና ለተለያዩ የግል ጋዜጣ አዘጋጆች መታሰርና መደብደብ ምክንያት የነበረ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ በህንድ የኢትዮጵያ ኢምባሲ ተመድቦ ተመሳሳይ ስራዎችን በመስራት ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል። ከዚህ ግለሰብ ጋር እርግቤ የተባለች ከአርቢስ ካምፓኒ ፊት ለፊት በሚገኘው የደህንነት መስሪአ ቤት ውስጥ ስትሰራ በነበረችበት ጊዜ የተቃዋሚ መሪዎችንና የተጠርጣሪ ግለሰቦችን ስልኮች በመጥለፍ የምትታወቅ ሰላይ አብራ መመደቧ ታውቋል።

ሌሎች ለተመሳሳይ ተልእኮ ከተላኩት መካከል ብሩና ሀይለጊዮርጊስ የሚባሉ ደህንነቶች የሚገኙ ሲሆን፣ የሰዎቹ ትክክለኛ አድራሻ እስካሁን አለመታወቁን መረጃው አመልክቷል።

ቅርብ ጊዜ ወዲህ ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ የገባው ወያኔ፣ ተጨማሪ የደህንነት አባላትን እያሰለጠ እንደሚገኝ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ የደህንነት አባለቱ ሲመረቁ በሱዳን፣ በጅቡቲ፣ በአውሮፓ፣ በሶማሊያና በተለያዩ የአረብ አገራት እንደሚመደቡ ታውቋል። ግለሰቦቹ ዋና ስራቸው የሚሆነው የግንቦት 7ትን እንቅስቃሴ መከታተል፣ የተለያዩ አባላትን በንቅናቄው ውስጥ በማስረግ ክፍፍል መፍጠርና በአጠቃላይ ድርጅቱ የሚዳከምበትን ስልት መቀየስ ነው።

ከደህንነት አባላቱ ጋር በመቀናጀት የሚሰራው የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሲሆን፣ መስሪያ ቤቱ በውጭ ያለውን የግንቦት7 ድጋፍ ለማድረቅ የተለያዩ ዘዴዎችን መቀየሱ ታውቃል። የዲያስፖራው አባላት ከወያኔ ድርጅቶች ገንዘብ እየተበደሩ በኢትዮጵያ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ወያኔ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ ሲሆን፣ እነዚህ አባላት በኢንቨስትመንት ስም የስለላ ስራም የሚሰሩ ናቸው። ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች እንደገለጹት የትግራይ ተወላጆች የሆኑ የዲያስፖራው አባላት ወደ አገር ተመልሰው የፈለጉትን ብድር ወስደው ስራ መጀመር የሚችሉ ሲሆን፣ የሌሎች ብሄር አባላት ግን ከወያኔ ተቋማት ገንዘብ ለማግኘት በቅድሚያ ለወያኔ ያላቸውን ታማኝነት በተለያዩ ስራዎች ማስመስከር ይጠበቅባቸዋል። የመጀመሪያውን ደረጃ ለማለፍ የሚጠይቀው መስፈርት በውጭ አገር ያሉትን የተቃዋሚ ደጋፊ አባላት ስም ዝርዝረና አድረሻ ለደህንነት ክፍሉ ማቀበል ሲሆን፣ ከዚያም በሁዋላ የተለያዩ የቅስቀሳ ስራዎችን እንዲሰሩ በደህንነት ክፍሉ የቤት ስራ ይሰጣቸዋል። በውጭ ጉዳይ መስራያ ቤት የተነደፈው አዲስ እቅድ ተግባራዊ በመሆን ላይ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ በቅርቡ እየታዩ አዳዲስ የዲያስፖራ አባላት የዚህ እቅድ ውጤቶች ናቸው ተብሎአል።

## በትግራይና በኦሮሞ ተማሪዎች መካከል . . . ከገጽ 1 የዞረ

በማድረግ አስተያየታቸውን የሰጡ ባለሙያዎች መኖራቸውን ሪፖርተራችን አክሎ ዘግቧል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔን አገዛዝ ማስወገድና በምትኩ ዲሞክራሲያዊ አስተዳዳር መመስረት እስካልተቻለ ድረስ አገራችን በዘር ግጭት መታመሷ የማይቀር መሆኑን ብዙዎች የሚናገሩት ነው። የግጭት አስወጋጅ ኮሚቴ የተባለው አለማቀፍ ተቋም በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የዘር ፍጅት ሊነሳ እንደሚችል በቅርቡ ማስጠንቀቁ ይታወቃል። ግንቦት7 አገራችንን ከዘረኞችና ከአምባገነኖች ለመታደግ የሞት ሽረት ትግል እያደረገ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ለአገራቸውና ለህዝባቸው ነጻነትና ደህንነት የሚያስቡ ሀይሎች ትግሉን እንዲቀላቀሉ ጥሪዎችን በማድረግ ላይ መሆኑ ይታወቃል።

**በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን**

**የፖስታሳጥን ቁጥር ፦** POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል

ከዝግጅት ክፍላችን

የዘንድሮዉ ግንቦት ምንኛ ቅጥ አጣ
ተገላገልን ስንል ከመንግሰቱ ጣጣ
ዘር ዘር የሚለን ሰዉ መለስ ብሎ መጣ

ከዚህ በላይ የቀረበው ግጥም የተገጠመዉ በ1983 ዓ.ም አገራችን ኢትዮጵያ ከኮለኔል መንግስቱ ወታደራዊ አምባገነን ስርአት ወደ መለስ ዜናዊ ዘረኛ አምባገነን ስርአት ሽግግር ባደረገችበት ወቅት ነበር። በወቅቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔን በሚገባ አያዉቀዉም ነበር። ሆኖም ነገሩ "እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል" ነዉና ከደርግ ይሻላል ብሎ በሩን ከፍቶ ያስጋባዉ ወያኔ ገና የእንግድነት ግዜዉን ሳይጨርስ አንተ የዚህ ዘር አንቺ የዚያ ዘር እያለ ሲጨቀጭቀዉ ነዉ ሐዘኑን በእንጉርጉሮ መግለፅ የለመደዉ የኢትዮጵያ ህዝብ "የዘንድሮዉ ግንቦት" እያለ ማንጎራጎር የጀመረዉ።

"ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል" ይሉ ነበር አበዉ ሲተርቱ። አዎ! ተረቱ ዛሬም ብዙ የአገራችን ሰዉ በቁም ከሚኖረዉ ባዶ ህይወት በህልፈተ ሞት የሚያገኘዉ ዘለዓለማዊ እረፍት የሚሻል መስሎ ሲታየዉ የሚተርተዉ ተረት ነዉ። በተለይ ዛሬ ዉሸትና ዝርፍያ የመሪዎች መለያ በሆነበትና የግለሰቦች ማንነት መለኪዉ የዘር ሀረግ በሆነበት የወያኔ ስርአት ዉስጥ "ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል" የማይል ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለንም። ካለም መንፈሱ ሞቶ ስጋዉ ብቻ የቀረ የወያኔ መጋዣ መሆን አለበት።

እንደዛሬዉ መረን የለቀቀ ባይሆንም ለሆድ ብቻ ማደር በአባቶቻችንም ዘመን የነበረ ችግር ነበር። እዉነቱን ለመናገር አባቶቻችን "ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል" ብለዉ የተረቱት እኛን ልጆቻቸዉን በምሳሌ ለማስተማር ብቻ አለነበረም። አባቶቻችን ይህንን ስሜት የሚቆረቁር ተረት የተረቱት የዘመናቸዉን ህብረተሰብ ዕድሜ ልክ በባርነት ከመኖር አንድ ቀን በነፃነት ኖሮ መሞት እንደሚሻል ለማስተማር ነበር። የሚገርመዉ እኛ ተማርን የምንለዉ ልጆቻቸዉ ግራ ተጋባን እንጂ አበዉማ - ሰዉ "ሰዉ" የሚባለዉ ሰብዓዊ መብቱ ተከብሮ በነፃነት ሲኖር ብቻ መሆኑ የገባቸዉ ሰዎች ነበሩ። ዛሬም ቢሆን በመንፈስ ሞቶ በአካል ብቻ አለሁ ብሎ ከሚያቅራራ ግማደ ሰዉ አንዱኑ ሞቶ የተቀበረ ሰዉ ይሻላል ብለዉ የሚያምኑ አያሌ ኢትዮጵያዉያን አሉ። ለዚህ ነዉ ዛሬም በኛ ዘመን "ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል" ብለን የምንተርተዉ እንጂ በገሀዱ አለምማ መቃብር ይሙቅ ይብረድ ማን ያየዉ አለ?

የኢትዮጵያ ህዝብ በብሔራዊ ነፃነቱ፤ በታሪኩና በወጉ ኮርቶ ለረጂም ግዜ ለመኖር የበቃዉ የአገሩን አንድነት በተከታታይ ከተነሱበት የዉጭ ወራሪዎች መጠበቅ በመቻሉ ነዉ። ዛሬ ግን ይህ የምንኮራበት አንድነት በአገር በቀል ተምቾች እየተናደ ነዉ። ዘንድሮማ ኢትዮጵያዊነታችን ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ ፍጡር የመሆናችን ምልክት የሆነዉ ነፃነታችን ሳይቀር በዘረኞች እየተረገጠ ነዉ። ለወትሮዉ እኛ ኢትዮጵያዉያን ጠላት ሲገላምጠን እንኳን የማንወድ ኩሩ ህዝብ ነበርን፤ ዛሬ ግን ከእኛዉ ዉስጥ የወጣ ጣላት አደባባይ ላይ ቆሞ አገራችንን እያንቋሸሸና እኛነታችንን እያሳነሰ ሲደነፋብን ሰምተን እንዳልሰማ እቤታችን ገብተን እንተኛለን።

በአፄ ቶዎድሮስና በአፄ ምኒልክ ዘመን ባዕዳን አገራችንን ጎብኝተዉ ሲመለሱ የጫማቸዉን አፈር እያራገፍን ነበር የምንሸኛቸዉ። ዛሬ ግን የጀግኖች አባቶቻችንን አፅም የተሸከመዉ መሬት ገፀ በረከት ሆኖ ለባዕዳን ሲቀርብ እያየን ምንም እንዳልተነካበት ሰዉ ተመልካቾች ሆነናል። የአገራችን ገበሬ የሚያርሰዉ መሬት አጥቶ በረሀብ ቸነፈር እየተገረፈ መለስ ዜናዊ ህንድና ቻይና የአገራቸዉን የምግብ ችግር እንዲያቃልሉ ለምለሙን የአገራችንን መሬት እየመረጠ አንካችሁ እያለ ነዉ። እነዚህ በህዝብ ብዛት በአለማችን አንደኛና ሁለተኛ የሆኑ አገሮች ኢትዮጵያ ዉስጥ ምግብ አምርተዉ የራሳቸዉን ህዝብ በቀለቡ ቁጥር የኢትዮጵያ ህዝብ የምግብ ችግር እየባሰበት ይሄዳል እንጂ ኢትዮጵያ ከዚህ አጉል የመሬት ሽያጭ የምታገኘዉ ምንም አይነት ጥቅም የለም። ስለዚህ እንደዚህ አይነቱ የሚያዋርደንና ዝንተ አለም የምግብ ለማኝ የሚያደርገን የክህደት ዉል በአንድ ግለሰብ ሲፈፀም 80 ሚሊዮን ህዝብ ዝም ብሎ ሊመለከት በፍፁም አይገባም።

ከላይ ከፍ ሲል እንደተገለፀዉ የሰዉ ልጅ በህይወት መኖሩ የሚረጋጋጠዉ ቆሞ በእግሩ ስለሄደ ብቻ አይደለም፤ አንድ ሰዉ ነፃነቱ እስካልተረጋገጠና ህይወቱን በራሱ ፈቃድ መምራት እስካልቻለ ድራስ አካሉ ቢንቀሳቀስም መንፈሱ የሞተ ነዉ። እዚህ ላይ በጣም የሚያሳዝነዉ ወያኔም ቢሆን የጀመረዉን የጥላቻና የአገር ማጥፋት ዘመቻ ያዝ ለቀቅ እያደረገ በዝግታ የሚገድለን መንፈሱ የሞተ ሰዉ አካሉ ዬቱንም ያክል ጠንካራ ቢሆን ባለጋራዉን ፊት ለፊት ገጥሞ ማሸነፍ እንደማይችል ስለሚገነዘብ ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ መለስ ዜናዊ በራሱ እጅ የፃፈዉ ህገመንግስት አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ አንድ እንደዚህ ይላል "ማንኛዉም ሰዉ ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና፣ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዉ"። የሚገርመዉ ህገ-መንግስቱ ብቻ ሳይሆን በቅርቡ በፓርላማ ፀድቆ ህግ የሆነዉ የምርጫ ስነ-ምግባር ደንብም እንደዚህ ይላል- "አንድ የፖለቲካ ፓርቲ፣ ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ የሕዝባዊ ድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባዎች ወይም የእግር ጉዞና ሰላማዊ ሰልፎች እንዳያደርግ ማገድ ወይም በሌላ በማንኛዉም መንገድ ማደናቀፍ የለበትም» ሆኖም በቅርቡ የአንድነት ፓርቲ አባላት ዳኛ ብርቱኳን ሚደቅሳ በግፍ የታሰሩበትን አንደኛ አመት ለማሰብ ሻማ አብርተዉ መስቀል አደባባይ ላይ ለመሰብሰብ ሲሞክሩ የመለስ ዜናዊ ዘበኞች አትችሉም ብለዉ ህገመንግስቱ ያገናፀፋቸዉን መብት በጠመንጃ ቀምተዋቸዋል።

እንግዲህ ይህ ህገመንግስቱ ለመለስ ዜናዊ ብቻ የፈቀደዉ ወንጀል የሚያሳየን የምርጫዉን ስነምግባር ደንብ እንደዋስትና የሚመለከቱ ኃይሎች በተለይም *"እኛ ታቀዋሚዎች በዚህ የምርጫ ስነምግባር ደንብ ካልተስማማን እስከ ምፅአት ቀን በምንም አንስማማም"* ብለዉ በራሳቸዉ ያሾፉት ግለሰብ የመለስ ዜናዊን ቃልአባይነት ለማረጋገጥ የግድ የምፅአት ቀን መጠበቅ እንደሌለባቸዉ ነዉ።

እዚህ ላይ አንድ ሳንጠቅስ ማለፍ የማንፈልገዉ ነገር አለ እሱም - የወያኔዉ ቃል አቀባይ ሽመልስ ከማል ሻማ ይዞ መሰብሰብ የህዝብን ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላል ብሎ የዋሸዉ አይን ያወጣ ዉሸት ነዉ። ሽመልስ ከማል ሞያዬ ብሎ የተሰማራበት የህግ መስክ በትክክል ገብቶት ከሆነ የህዝብ ደህንነት አደጋ ላይ የሚወድቀዉ ህግ የበላይ መሆኑ ቀርቶ የዘረኞች መጠቀሚያ ሲሆን ነዉ እንጂ ሠላማዊ ሠልፈኞች ሻማ ስላበሩ አይደለም። ደግሞስ 200 ሠላማዊ ሠልፈኛ በአንድ ጀምበር የጨፈጨፈዉ ወያኔ ከመቼ ወዲህ ነዉ ለህዝብ ደኅንነት መጨነቅ የጀመረዉ? ሽመልስ ከማል ገና በወጣትነቱ ጃጅቶ ነዉ እንጂ ጌታዉ መለስ ዜናዊና እመቤቱ አዜብ መስፍን የ1997ቱን የዓለም ኤድስ ቀን ያከበሩት ሻማ ይዘዉ እዚያዉ መስቀል አደባባይ ላይ አልነበር? ወይስ የነሱ ሻማ አያቃጥልም?

የእስከዛሬዉ ትግላችን ከወያኔ ጋር መሆኑ ቀርቶ እርስ በርሳችን ስለነበር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለመለስ ዜናዊ የሥልጣን ዘመን መራዘም አስተወፅዖ ስናደርግ ቆይተናል። ዛሬ ግን አብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ ወዳጅና ጠላቱን በሚገባ ለይቶ ጠላቱን መፋለም ጀምሯል። ከሰሞኑ የወያኔን ሰፈር ያናጋዉና መለስ ዜናዊን የአደባባይ ላይ ተሳዳቢ ያደረገዉ ይሄዉ የነፃነት ኃይሎች በተለይም የግንቦት ሰባት የነፃነት፤ የፍትህና፤ የዲሞክራሲ ንቅናቄ በአገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ በፍጥነት እየተጠናከረ መምጣት ነዉ። የሰሞኑ የወያኔ ጩኸትና ልቅሶማ ጭራሽ መርዶ ያረዷቸዉ ይመስል ኮሽ ባለ ቁጥር ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት ጀምረዋል። አንዴ ሊገድሉን ነዉ አንዴ ህንፃዉን ሁሉ ሊያፈርሱት ነዉ እየለ የባጥ የቆጡን የሚዘባርቀዉ መለስ ዜናዊ እረስቶት ይሆናል እንጂ እሱ እራሱ እኮነዉ እባክህ ተብሎ ሲለመን "መንገዱን ጨርቅ ያርግላችሁ" ያለዉ!

**የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ** ጭንቀትህ፤መከራህና መገፋትህ አንገፍግፏቸዉ በምሬት የተነሱ ልጆችህ የድርጅት ብቃታቸዉን አጎልብተዉ የባርነት ዘመን አበቃ ብለዉ የመጨረሻዉን የነፃነት ደወል እየደወሉ ነዉ፤እንግዲህ ከዛሬ በኋላ ጆሮህ የሚሰማዉ የልጆችህን የነፃነት ደወል አይንህ አተኩሮ የሚመለከተዉ ደግሞ ከወያኔ ባሻገር የሚመሰረተዉን እኩልነት የሰፈነበት ስርአት መሆን አለበት።

ወያኔ የሚያሰቃየዉ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ስለሆነ ወያኔን ማስወገድም የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የግልና የጋራ ሐላፊነት መሆን አለበት። ትግላችን በምርጫ ስም የወያኔን እድሜ ለማራዘም ሳይሆን ሰብዓዊ መብታችንንና ነፃነታችንን ለማስከበር ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ የወያኔ ዘረኞች ጫካ ዉስጥ ሆነዉ ያቀዱትን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት ዕቅድ አመቺ ግዜ እየጠበቁ ተግባራዊ ባደረጉ ቁጥር ለአንድ ሰሞን ብቻ "ኡኡ" እያልን የምናልፋቸዉ ከሆነ እቺን ከአባቶቻችን የተረከብናትን ኢትዮጵያ ለመጪዉ ትዉልድ ማስረከብ ቀርቶ እኛዉ እራሳችን ሞተን ላንቀበርባት እንችላለን።

ዘረኛዉ የወያኔ ስርአት ተወግዶ በነፃነት፤ በሠላምና በእኩልነት መኖር የማይፈልግ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለንም።ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ የዜግነት መለኪያዉ የወያኔ አባል መሆን የሰዉነት መለኪያዉ ደግሞ የዘር ሐረግ ሆኗል። ይህ ከሰብዓዊነት ዉጭ የሆነ ኋላ ቀር አሰራር ያላንገሸገሸዉ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ብለን አናምንም።እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚጠቁመን ኢትዮጵያ ዉስጥ ስር ነቀል ለዉጥ በአጭር ግዜ ዉስጥ ማየት የማይመኝ ኢትዮጵያዊ እንደሌለ ነዉ። ታድያ ምንድነዉ የምንጠብቀዉ? ወያኔ እንደሆነ ዘረኝነቱ፤ ከፋፋይነቱና አገር ሻጭነቱ ከቀን ወደ ቀን እየከፋ ይሄዳል እንጂ ስለጠላነዉና አንፈልግህም ስላልነዉ ብቻ የሚወገድ የዋዛ ኃይል አይደለም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔን ብዙ ታግሶታል ከዛሬ ነገ እያለም ብዙ ግዜ ሰጥቶታል፤ ሆኖም የወያኔ ምላሽ ንቀት፤ምን ያደርጉኛል የሚል ትዕቢትና በበደል ላይ በደል ብቻ ሆኗል። ስለዚህ ካሁን በኋላ ከወያኔ ጋር በእንካ ሰላንቲያ የምናጠፋዉ ግዜ ሊኖር አይገባም። ወቅቱ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከነፃነት ኃይሎች ጋር በጋራ የሚቆምበት ወቅት ነዉ። ይህ የነፃነት ትግል አንዳንዶቻችንን ለእስር ሊዳርገን አንዳንዶቻችንን ደግሞ የህይወት መስዋዕትነት ሊያስከፍለን ይችላል። ሆኖም ወያኔዎች ሊገዙንና ሊረግጡን የከፈሉትን የህይወት መስዋዕትነት እኛ ነፃነታችንን ለማስከበርና አገራችንን ከመበታተን ለማዳን መክፈል በፍፁም አያቅተንም። ስለዚህ ይህንን መልዕክት የምታነብ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ወያኔን ለአንዴም ለመጨረሻም የምናስወግድበት ግዜ ሩቅ አይደለምና ለወሳኙ ፍልሚያ በያለህበት በተጠንቀቅ ቁም!

## የወያኔ ካድሬዎች በርካታ የደሀ አርሶ አደር . . . ከገጽ 1 የዞረ

የመሬት ዝረፊያ፣ ስብሀት ነጋን፣ ስዩም መስፍንን፣ አባይ ጸሀየንና ሌሎችንም ከፍተኛ ባለስልጣኖች ማካተቱትን የውስጥ ምንጮችን ዋቢ በማድረግ ዘጋቢያችን ገልጿል። በእነዚህ ሰዎች የተዘረጋው ሰንሰለት በዋና ዋና የአገሪቱ መሬቶች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን፣ በመካከሉ የሙስናውን ነገር የሚያስፈጽሙ በርካታ የትግራይ ተወላጅ ካድሬዎች ይገኛሉ። ካድሬዎቹ በፈለጉት ጊዜና በፈለጉት ቦታ ላይ ሰፋፊ መሬቶችን ከደሀው አርሶ አደር መቀማት የሚችሉ ሲሆን፣ የቀሙትን መሬት ያለምንም ውጣ ውረድ በባለቤትነት የሚመዘግቡላቸው ታማኝ ካድሬዎች በመሬት አስተዳደር ባለስልጣኖች ውስጥ ተሰግስገው ይገኛሉ። እነዚህ ጉዳይ አስፈጻሚዎች በቀጥታ የተባሉትን ከማድረግ ውጭ ሌላ ተቃውሞ የማያነሱ ሲሆን፣ ሌሎች ዜጎች የመሬት ባለቤት ለመሆን እስከ አምስት አመትና ከዚያ በላይ የሚወስድባቸውን ጊዜ ለእነዚህ የዘመኑ የወያኔ ካድሬ ኢንቨስተሮች በቀናት ውስጥ እንዲያልቅላቸው ይደረጋል። ከደሀው ገበሬ በአነስተኛ የካሳ ክፍያ ነጥቀው የመሬት ባለቤት የሆኑት ካድሬ ኢንቨስተሮች በፊናቸው ታዋቂ የውጭ አገር ባለሀብቶች ሲመጡ በሚሊዮኖች በሚቆጠር ገንዘብ እንደሚሸጡላቸው ታውቋል። የሽያጩም ገንዘብም ከታማኝ ካድሬዎች እስከነመለስና አዜብ ድረስ በተዘረጋው የቅብብል ሰንሰለት እንደሚተላለፍ ዘጋቢአችን አክሎ ገልጿል።

መሬቱን ከታማኝ ካድሬዎች የገዙ ባለሀብቶች በቦታው ላይ ምን እንደሚሰሩ የሚቆጣጠራቸው አካል አለመኖሩን የገለጸው ዘጋቢያችን፣ ብዙዎቹ የህንጻ ግንባታ ከማድረግ ወይም መልሰው ለሌላ ባለሀብት በመሸጥ ትርፍ ከማጋበስ ውጭ የረባ ስራ አይሰሩበትም። በሌላ በኩል ደግሞ ከአገዛዙ ታማኝ ካድሬዎች መሬቶችን ያልገዙ ባለሃብቶች በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተፈለገውን ስራ በቦታው ላይ አልሰራችሁም በሚል ምክንያት መሬታቸው እየተቀማ ለእነዚህ የወያኔ ካድሬዎች እንደሚሰጥ ለማረጋገጥ ተችሎአል።

በተያያዘ ዜናም የቻይናና የህንድ ኩባንያዎች በአለም ላይ ተሰምቶ በማይታውቅ ዋጋ የሚገዙት የመሬት ሽያጭ ሰፊ የሙስና ስራ የሚሰራበት መሆኑ ታውቋል። የህንድ፣ የቻይናና ያረብ አገሮች ባለሀብቶች በአለም ገበያ ተሰሙቶም ታይቶም በማያውቅ እጅግ አነስተኛ በሆነ ገንዘብ መሬት የሚገዙት የእውነተኛውን ዋጋ ገንዘብ ለወያኔ ባለስልጣናት በሙስና መልክ ስለሚያዛውሩ መሆኑን የግንቦት7 የመረጃ ምንጮች ደርሰውበታል። እንደምንጮቹ ዘገባ፣ ማንኛውም በመሬት ግዥው የተሰማራ የውጪ አገር ባለሃብት በሄክታር አንድ ዶላር ከ30 ሳንቲም እንዲከፍል ከተደረገ ቦኋላ በአፍሴል ለመንግሥት እንዲከፍል ከሚደረገው ጠቅላላ የመሬት ሽያጭ በተጨማሪ ከ10 እስከ 20 እጥፍ ሽያጩን ለሚያመቻቹና ለሚፈቅዱ ቱባ ቱባ የወያኔ ባለሥልጣናት በኮሚሽን መልክ ይከፈላቸዋልል። በዚህም መሰረት እስከ ዛሬ ከ13 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገንዘብ በተለይ ከአረብ አገር እና ከህንድ ከመጡ መሬት ተቃራጮች በሼህ አላሙዲን አማካይነት ለወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ፤ ለደህንነት ሃላፊው ለጌታቸው አሰፋ እና ለክልሎች ጉዳይ ሃላፊ ዱባይ እና ሳውዲ አርቢያ በሚገኙ የሼሁ ባንክ ሂሳብ ገቢ እንደተደረገላቸው ለደህንነት መስሪያቤት ቅርበት ያላቸው ምንጮቻችን አረጋግጠዋል። ከዚህም በተጨማሪ ከጅምላው የመሬት ሺያጭ የሚገኘው ገንዘብ የሚቆጣጠሩት መሬቱን የተነጠቁ ክልሎች ሳይሆኑ እነ አዜብ መስፍንና መሰሎቿ እንደሆኑ ታውቆአል። ይህንን ከፍተኛ ዝርፊያ የሚፈጸምበትን የመሬት ሽያጭ በመደለል ከሚታወቁት ከሼህ አላሙዲን በተጨማሪ በቻይናዎቹ በኩል ሀይለኪሮስ ገሰሰ የተባለው የህወሀት ካድሬ አምባሳደር ሲሆን፣ በህንዶች በኩል ደግሞ ከህዝብ በተዘረፈ ንብረት የተሰሩ የአምሰት ዘመናዊ ቤቶች ባሌበት የሆነቺው የቀድሞዋ ትምህርት ሚኒስትር ገነት ዘውዴ እና በእርሷ ስር ያለው ታማኝ የህወሀት ካድሬ እንደሆኑ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

የአለማቀፍ የመገናኛ ብዙሀንና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በመሬቱ ዋጋ ላይ ያለቸውን ነቀፌታ የገለጹ ቢሆንም ቻይናውያንና ህንዳውያን መሬቱን የገዛነው በአገሪቱ ባለው ትክክለኛ ዋጋ መሰረት ነው እያሉ በመከራከር ላይ ናቸው። በአንድ ድህረገጽ ላይ በቀረበ መረጃ "ቻይናዎቹ እኛ የኢትዮጵያን መሬት እየዘረፍን አይደለም፣ በአንድ መሬት ሁለት አይነት ክፍያ ፈጽሙ እየተባልን ነው። ለአንደኛው ክፍያ ደረሰኝ ይሰጠናል፣ ለሌላው ክፍያ ግን ደረሰኝ አይሰጠንም፣ በዚህም የተነሳ ሂሳብ ለማወራረድ እንኳን ተቸግረናል። እኛ ተገቢ ክፍያ እየፈጸምን ነው ብለን እናስባለን፣ ችግሩ ሌላ ቦታ ከሆነ እነርሱን መጠየቁ ይሻላል" ብለው መናገራቸው ይታወሳል።

በዚህ አየር በአየር የመሬት ዝረፊያ የከበሩት ጥቂት የትግራይ ተወላጅ ካድሬዎች ሲሆኑ፣ እነርሱ በአንድ ቀን ከሚሊየነርነት ተርታ ሲሰለፉ መሬቱን እየተቀማ ያለው ደሀው አርሶ አደር ግን በወራት እድሜ ውስጥ የሚበላው አጥቶ ለጎዳና ተዳዳሪነት በመጋለጥ ላይ ነው። አንዳንድ በቀጥታ ወደ እርሻ የገቡ ቻይናውያን መሬታቸው የተወሰደባቸውን ገበሬዎች ቀጥረው የሚያሰሩ ሲሆን፣ ለገበሬዎች የሚከፍሉት ዋጋ አነስተኛ መሆን ገበሬዎች ከመሬታችንም ከኑሮዋችንም ሳንሆን ቀረን እያሉ በማማረር ላይ ናቸው።

በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ውስጥ እየተደረገ ያለውን ዘርፊያ ለማስቆም ተቃውሞዋቸውን በቻይ፣ በህንድ እና በሌሎችም ኤምባሲዎች ላይ ማሰማት እንደሚኖርባቸው ብዙዎች ይስማማሉ።

## ወያኔ በድጋሚ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ አደረገ፣ የህዝቡን ኑሮ አሁን ካለበት ደረጃም የባሰ ያደርገዋል ተብሎአል

የነዳጅን ዋጋ በየጊዜው በመጨመር የኑሮ ውድነቱን እያባባሰው የሚገኘው ወያኔ ፣የአለም ነዳጅ ዋጋ እየወረደ ባለበት በአሁኑ ሰአት ዋጋ መጨመሩን የአዲስ አበባዋ ዘጋቢአችን ገልጻለች። አዲሱን የዋጋ ጭማሪ ተከትሎ የትራንስፖርትና የሌሎች እቃዎች ዋጋ እንደሚጨምርና ህዝቡ አሁን ከገባበት የኑሮ አዘቅት ወደ በለጠ አዘቅት እንደሚገባ ዘግባለች። አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ነጋዴ ሲናገሩ፣ " እኛ ነዳጅ እንደቀነሰ ነበር የምንሰማው፣ መንግስት ግን ዋጋ ይጨምርብናል። እኔ በምን አይነት መንግሰት እንደምንገዛ ሊገባን አልቻለም። በህዝቡ ስቃይ ይደሰታል ማለት ነው?" ብለዋል። ነጋዴው የነዳጅ ዋጋ ጭማሪውን ተከትሎ በእቃዎች ላይ የዋጋ መጨመር እንደሚኖር ጠቁመው፣ የህዝቡ ገቢ እየተዳከመ ባለበት ሁኔታ ፣ ውድ የሆኑትን እቃዎችን ሊገዙ የሚችሉት የዘመኑ ሰዎች ካልሆኑ በስተቀር ሌላ ሰው ሊሆን አይችልም ብለዋል።

የወያኔ መሪዎች እነርሱና በዙሪያቸው የተኮለኮሉ ጥቂት ሆዳም ካድሬዎች የሚኖሩትን የተንደላቀቀ ኑሮ እየተመለከቱ፣ ህዝቡም እነደነርሱ የሚኖር እየመሰላቸው የሚወስዱት እርምጃ የአገሪቱን ደህንነት አደጋ ውስጥ እየከተተው ነው።

## ወያኔ በኢትዮጵያ የተከሰተውን ረሀብ ለመደበቅ ሙከራ እያደረገ ነው ሲል ቢቢሲ ዘገበ

አለማቀፉ የዜና አውታር ቢቢሲ ባለፈው ሳምንት ባሰራጨው ዘገባ እንደገለጸው የወያኔው አገዛዝ ለፖለቲካ ምስሉ ሲል በኢትዮጵያ ያለውን አስከፊ ረሀብ ለመደበቅ እየሞከረ ነው። በአሜሪካ መንግስት የሚደጎመው የቅድመ ማስጠንቀቂያ ክፍል በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በመጪዎቹ ወራቶች ከፍተኛ የሆነ የምግብ እጥረት ያጋጥማቸዋል ብሎ ማስጠንቀቂያ ቢሰጥም፣ ወያኔ ግን በተለመደው ቅጥፈቱ ጉዳዩን ለማጣጣል መሞከሩን ቢቢሲ ገልጿል። የቅድመ ማስጠንቀቂያው ይፋ ባደረገው መረጃ ከጥር እስከ መጋቢት በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የምግብ እጥረት እንደሚከሰት የገለጸ ሲሆን፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅና በደቡብ ምእራብ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ክፉኛ እንደሚጠቁ አስጠንቅቋል።

የወያኔው የዘራፊዎች ቡድን ረሀብን ተመልከቶ የሚነሱ ጥያቄዎችን በተደጋጋሚ በማጣጣል የሚታወቅ ሲሆን፣ የፖለቲካ ምስሉ ከሚበላሽ ሚሊዮኖች በረሀብ ቢረግፉ እንደሚመርጥ ተደጋግሞ መገለጹ ይታወሳል። አሁን ተከሰተ የተባለው ረሀብ ከዚህ ቀደም ከተከሰቱት ረሀቦች የሚለይበት አንዱ ገጽታ፣ የአሁኑ ረሀብ የትግራይን ክልል አለማካተቱ ነው ያሉን አንድ የግብርና ባለሙያ፣ የጋምቤላ አካባቢ ህዝብ በትግራይ ህዝብ ፋንታ በረሀብ እንዲገረፍ እየተደረገ ነው ብለዋል።

አገራችን ላለፉት 19 አመታት አንድም ቀን ከረሀብ ለመላቀቅ አለመቻሉዋን ያስታወሱት ባለሙያው፣ የውጭ አገር እርዳታ በገፍ ባይላክ ኖሮ በርካታ ህዝብ እንደቅጠል በረገፈ ነበር ሲሉ አክለዋል። በአሁኑ ጊዜ ከ15 ሚሊዮን በላይ ህዝብ በውጭ አገራት በሚሰጥ እርዳታ እየተደጎመ ሲሆን፣ ይህም አሀዝ እስካሁን በኢትዮጵያ ታሪክ ከታዩት የርሀብተኞች ቁጥር ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛው ነው። አምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ ሁሌም በመንግስቱና በንጉሱ ዘመን የነበረውን የረሀብተኛ ቁጥር እያነጻጸረ የአሁኑ ሁኔታ የተሻለ ነው እያለ ለማደናገር ቢሞክርም፣ እውነታው ይህ አለመሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ ። እንዳሁኑ ጊዜ የውጭ እርዳታ ባልጎረፈባቸው ሁለት ስርአቶች የነበረው የረሀብተኛ ቁጥር ከአጠቃላይ ህዝቡ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር ከ10 በመቶ እንደማይዘል መረጃዎች ሲያመለክቱ በአሁኑ ጊዜ ያለው አሀዝ ግን ከ20 በመቶ በላይ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ያለፉት ሁለት ስርአቶች ለወያኔ እንደሚደረገው አይነት አለማቀፍ ድጋፍ ቢደረግላቸው ኖሮ ረሀብ የሚባል ነገር ባልተከሰተ ነበር የሚሉት ባለሙያዎች፣ የወያኔ ቡድን ይህን ያህል ድጋፍ እየተደረገለት እንኳን አገሪቱን መግቦ ማደር አለመቻሉ አገዛዙ በሁሉም መስክ ፍሬ አልባ እየሆነ መምጣቱን ያሳያል ብለዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን** g7radio@ginbot7.org **ወይም** በስልክ ቁጥር **0044- 203-286- 9661**